


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከኦክቶበር 21-31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ እና

# ከኖቬምበር 1-10፣11-20 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ ትንበያ እና

# ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2025

አዲስ አበባ

ስልክ+2511155383944ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት ለበጋ ዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ የተሻላ ገጽታ ነበራቸዉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሁኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ እንዲሁም በክረምት ወቅት ዝናብ ሲያገኙ የነበሩት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻላ ገጽታ ነበራቸዉ፡፡ በመሆኑም፤ በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች፣ የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ ሶማሌ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ጠንከር ያለ የደመና ክምችት ተስተውሎባቸዋል። በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎችም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ጠንካራና ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በተጨማሪም በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል ጎሬ 21.4፣ 26.7፣ 31.9፣ ሮቤ 17.2፣አቦቦ 20.6፣ 37.4፣ አማን 56.6፣ አርጆ 26.8፣ 18.6፣ 22፣ ቦሬ 23.4፣ ቡለን 32.2፣ 21፣ ቡሬ 70.7፣ 25.5፣ ቻግኒ 22.8፣ 17፣ ጨዋቃ 16፣ 30፣16.4፣ ደምቢ ዶሎ 23.5፣ 18፣ ዶሎመና 30.4፣ ጋምቤላ 26.7፣ ፊኙዶ 25.5፣ ጊዳ አያና 17.3፣ 22.9፣ ጃራ 25.7፣ ጂንካ 15.1፣ 37.7፣ ቀብሪ ዳሃር 15.3፣ ማጂ 18.8፣ ሞያሌ 23.4፣ ነጆ 34.5፣ ሳዉላ 31.2፣ ሻሁራ 16.1፣ ሽሬ 15.9፣ ያቤሎ 23.4፣ 24.3፣ አቦ ሞሪንጋ 52፣ አጋሮ 18፣ አሺ 15.4፣ ቢላም ቢሎ 36፣ ቦርቃ 42.3፣ ቡልቂ 25.9፣ 19.4፣ 25.1፣ ፎጉ ሌቃ 20፣ ጌጫ 17፣ 19፣ ጉብቲ 24.1፣ ቅዳሜ ገበያ 47.8፣ 28.4፣ ኦንጋ 28.8፣ ሲቦ 18.4፣ 15.7፣ ትንሹ ሜጢ 25.6፣ ያንፉ 20.4፣ ዩና 24.9፣ እንዲሁም መንደር ሰባት 35.7ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በአስራ አምስት (15) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታች በሁኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች እንዲሁም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 35.7- 70.4 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ35 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ቡሬ፣ አማን፣ አቦ ሞሪንጋ፣ ቅዳሜ ገበያ፣ ቦረቃ፣ ጅንካ፣ አቦቦ፣ ቢላም ቢሎ፣ መንደር ሰባት፣ ነጆ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ ሲያገኙ የነበሩት


የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጥን ያለዉ አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በሰሜን የሀገሪቱ አከባቢዎች በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 1 )፡፡





ምስል፡1 ከኦክቶበር 21-31 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት አከባቢዎች የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ እና ዶሎ ዞኖች ላይ ከ16-111 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-7 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ1 እና 2)፡፡ በተመሳሳይ ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜንና ምዕራብ ጎጃም፣ የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ ዞኖች፣ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ የወላይታ እና ጌዲዮ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ31-111 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡


በሌላ በኩል የሰሜን፣ መከከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ፋንቲ፣ ሃሪና ጋቢ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ሃዲያ፣ ስልጤ፣ ከንባታ፣ የሃላባ፣ የም፣ ቀቤና ዞኖች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከ6-30 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ከሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ከኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ዳዋ፣ ሊበን፣ ቆራሂ፣ ዞኖች ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡

በሌላ በኩል ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት የተስተዋል ሲሆን ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች ከተመዘገበባቸዉ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል ደብረ ብርሃን፣ ሐሮማያ፣ አለም ከተማ፣ ቡሂ፣ ጅግጅጋ፣ ሾላ ገበያ፣ አምባ ማሪያም፣ ወገል ጤና ይገኙበታል፡፡

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በቦረና፤ በጉጂ እና በደቡብ ክልል ደቡባዊ ዞኖች የነበረው እርጥበት ለተዘሩ የበጋ ሰብሎች ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ሲሆን በአርብቶ አደሩ አካባቢ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልና የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማችት አዎንታዊ ሚና ነበረው። በአንጻሩም ከክረምት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ በነበሩት በደቡብ ምዕራብ አጋማሽ የመኸር አብቃይ አከባቢዎች የተገኘው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ፣ ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለነበሩ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እና ለፍራፍሬዎች የተሟላ እድገት እንዲኖራቸዉ ከማድረግ አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው። እንዲሁም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች የነበረው ደረቅ ሁኔታ የደረሱ እና በመሰብሰብ ላይ ለሚገኙ እንደ ሰሊጥ፣ ጤፍ እና ስንዴ የመሳሰሉ ሰብሎችን ለመሰብሰብ አዎንታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 4) ።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ኦክቶበር ሶስተኛው አሥር ቀናት በአብዛኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦጋዴን፣ በመካከለኛው እና በታችኛው ስምጥሸለቆ፣ አባይ እንዲሁም ኦሞ ጊቤ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት የነበራቸው ሲሆን በመካከለኛው እና በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ እና በላይኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ተፋሰሶች የተሻለ የውሃ ግብዓት እንደ ነበር የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ ተከዜ፣ አይሻ፣ አዋሽ፣ በላይኛው አባይ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞ ጊቤ እና ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5) ።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. መግቢያ


የበጋ ወቅት ከኦክቶበር እስከ ጃንዋሪ ያሉትን ወራት የሚያካትት ሲሆን፤ ለደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው፡፡ የበጋ ወቅት ከዓመታዊ የዝናብ መጠኑ እስከ 45% የሚደረሰውን የሚሸፍን ሲሆን ከበልግ ቀጥሎ የተሻለ ዝናብ የሚኖርበት ወቅት ነው። በኖቬምበር ወር የበጋው ዝናብ በአብዛኛዉ በደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ላይ የሚወሰን በመሆኑ የደቡብ ኦሮሚያ፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ዞኖች ከ5-10 ቀናት ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን በመጠን ከ 50-100 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም የሶማሌ ደቡባዊ ክፍል ከ5-10 ቀናት ዝናብ የሚያገኝ ሲሆን፣ የተቀሩት የሰሜን ምሥራቅ እና የምዕራብ ቆላማ አካባቢዎች ከ2 ለማይበልጡ ቀናት አነስተኛ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ በመጠን 3-25 ሚ.ሜ ዝናብ ያገኛሉ።

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በይበልጥ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ያገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ይስተዋላል፡ ፡ በተጨማሪም በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ እና ደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ይሄዳሉ፡፡


### 2.1 እ.ኤ.አ ከኖቬበር 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም የተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት የምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ፣ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በደቡብ ምዕራብ፣ ደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ


አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ የሚደርስ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ መካከለኛዉና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ጥቂት የሰሜን፣ ደቡብ ወሎ እና ዋግ ህምራ ዞኖች፣ የሰሜን ምዕራብና መካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች፣ የምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 12-10, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 1-10, 2025 የሚኖረዉ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

Ethiopian Meteorology Institute

በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ እንደሚሄድ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በደብረ ብርሃን፣ አርሲ ሮቤ፣ አዳባ፣ ደሴ፣ ባሌሮቤ፤ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ፣ አደሌ፣ አምባ ማሪያም፣ ኮምቦልቻ፣ አንኮበር በአብዛኛዉ ቀናቶች ለይ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 8)።

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን |
| አሮሚያ | ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ጃረር፣ ዶሎ፣ ነጎብ፣ ቆራሂ፣ ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ዳዋ፣ እና ሊበን ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ዞኖች | | |
| አሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኘዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |

| ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎች | | |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም የአዊ፣ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ጥቂት የሰሜን እና ደቡብ ወሎ እና የዋግ ህምራ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | በጥቂት የሰሜን ምዕራብ እና የመካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | በጥቂት የጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ፋፈን እና የኤረር ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.2 እ.ኤ.አ ከኖቬበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዉቹ የኖቬምበር ሁለተኛዉ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም የተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና የምስራቅ ቦረና፣ የምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀጣይነት ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ ይሁን እንጂ በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ፣ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ሰሜን የሀገሪቱ አከባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ።

## 2.3 እ.አ.አ ከኖቬበር 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው የክረምቱ ቀጣይነት ያለዉ እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት አርብቶ አደሮች እና ከፊል የአርብቶ አደር ዞኖች ላይ የሚጠበቀው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት በአካባቢው ለሚከናወነዉ የግብርና እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ሠንጠረ ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ ፣ ጉጂ፣ ጃረር፣ ዶሎ፣ ነጎብ፣ ቆራሂ፣ ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ ፣ደቡብ ኦሞ፣ ዳዋ፣ ሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• በደጋማ አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገት<br>• ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • የአፈር ዉስጥ እርጥበት መጠነኛ መሆን<br>• ከፍተኛ ትነት | • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>• የእንስሳት መኖ ከሰበል ተረፈ ምርት ማሰባሰብ እና ማከማቸት<br>• የመጠጥ ውሃን ከብክለት መጠበቅና አክሞ መጠቀም |
| **የመኸር ሰብል አምራች ዞኖች** | | | | |
| የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ፣አኝዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር፣ ፣ኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ ፣ምዕራብ ኦሞ ፣ የወላይታ፣ ጎፋ እና ጌድዮ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • በመኸር ወቅት መጨረሻ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች እድገት<br>• ዘግይተው ተዘርተው ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ ሰብሎች<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሟላት<br>• የውርጭ ስጋት መቀነስ | • የደረሱ ሰብሎች ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ<br>• ከእርጥበትና ሙቀት የተነሳ የዋግ በሽታ ስጋት መጨመር | • የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች መሰብሰብ<br>• የጥራጥሬ ሰብሎች (ሽንብራ እና ጓያ) እድገትን መከታተል መዝራት<br>• በደጋና በውይን አደጋ አካባቢ የሰብል በሽታ ክትትል ማድረግ |
| **ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚጠበቅባቸው ዞኖች** | | | | |
| ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን | • ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• ዘግይተው ተዘርተው ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ ሰብሎች እድገት | • በመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ | • የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የመሰብሰብና በአግባቡ የመከመር ተግባራትን |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የአዊ፣ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የሰሜን ሸዋ፣ ጥቂት የሰሜን እና ደቡብ ወሎ እና የዋግ ህምራ ዞኖች፣ በጥቂት የሰሜን ምዕራብ እና የመካከለኛዉ ትግራይ ዞኖች፣ በጥቂት የጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ፋፊን እና የኤረር ዞኖች፣አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | ያለዉ እርጥበት | • በበጋ መስኖ ለሚከናውን የግብርና እንቅስቃሴ | አነስተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ | ማከናወን |

## 2.4 እ.ኤ.አ ከኖቬበር 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀትሉት ኖቬምበር የመጀመርያዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛው የበጋ እርጠጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን የተቀሩት ተፋሰሶች ዝቅተኛ እርጥበት ይኖራቸዋል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘረፉ አካላት የቀረቡትን ተፋሰስ ተኮር የውሀ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም አሉታዊ ሁኔታን ለመቀነስ እና እንዲሁም መልካም አጋጣሚዎችን በተሻለ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ኦጋዴን፣ ፣ መካከለኛው እና ታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት የላይኛው አባይ | መካከለኛ የእርጥበት መጠን | • የጎርፍ ስጋት መቀነስ<br>• ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ እንዲሁም ለመጠጥ ውሃ መጠነኛ የውኃ አቅርቦት መኖር | • አንጻራዊ የትነት መጨመር | • የሚገኘውን ውሃ ከብክነት እና ከብክለት መጠበቅ<br>• የዝናብ ውሀ ማሰባሰብና ማጠራቀም |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ አባይ፣ መረብጋሽ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ እና ተከዜ | ከመጠነኛ እስከ ደረቅ ሁኔታ | • የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ | • ከፍተኛ ትነት | • የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም<br>• የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል ማሰባሰብ<br>• የሚገኘውን መጠነኛ የዝናበ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት መከላከል |